ቀን ህዳር 16, 2017 ዓ.ም.

ቁጥር ቦዳ/1155/17

የኢትዮጵያ አይነስውራን ብሔራዊ ማኅበር

ዳሽን ባንክ አ.ማ

አግሪ ሰርቪስ ኢትዮጵያ

የአዲስ አበባ ነጋዴ ሴቶች ማህበር

የኢትዮላይፍ ኤንድ ጄኔራል ኢንሹራንስ አ.ማ

ፕሮጃይኒስት

አቶ ኃይሉ ወንድአፍራሽ ወልደአማኑኤል

አቶ ተወልደብርሃን ገ/ጻዲቅ ገ/ስላሴ

አቶ አየለ ቦጋለ ገዳሙ

አቶ መንግስቱ መሐሩ

አቶ ሰለሞን ወ/ጊዮርጊስ

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፡- **31ኛ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥሪ**

በኢ.ፌ.ድ.ሪ ንግድ ህግ ቁጥር 1243/2013 አንቀፅ 366(1)፣367(2)፣398 እና 370 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ የተሻሻለ መመስረቻ ፅሁፍ አንቀፅ 21 መሰረት የልዩ ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 31ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ታህሳስ 12 ቀን 2017 ዓ.ም. ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት ጀምሮ 22 አካባቢ በሚገኘው ኒው ዴይ ሆቴል ይካሄዳል፡፡ በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በዕለቱ በጉባኤዎቹ ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን ያስተላልፋል፡፡

1. **አክሲዮን ማህበሩን የተመለከቱ መረጃዎች**

1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት አድራሻ፡- አዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 04 የቤት ቁጥር አዲስ የሚገኝበት አካባቢ 22 ከጎላጎል ወደ ቦሌ በሚወስደው መንገድ ኒው ዴይ ሆቴል አጠገብ ሲሆን የማህበሩ ድረገጽ አድራሻ www.liyumfi.com ነው፡፡

1.2. የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፡- MFI/034/2011

1.3. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ(ካፒታል)፡-75,000,000

ልዩ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አ.ማ Liyu Microfinance Institution S.C

1.4. የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ(ካፒታል)፡-75,000,000

2. **የ31ኛው የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች**

1. የ2023/24 በጀት ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ማጽደቅ
2. የ2023/24 በጀት ዓመት የውጭ ኦዲተር የኦዲት ሪፖርት መስማትና ተወያይቶ ማፅደቅ
3. የ2023/24 ሂሳብ ዓመት ትርፍ ክፍፍል ላይ ተወያይቶ መወሰን
4. የውጪ ኦዲተሮችን መሾምና ክፍያቸውን መወሰን

3. **ማሳሰቢያ**

3.1. በጉባኤው ላይ መገኘት የማትችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁ ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ህግ አንቀፅ 377 መሰረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሶስት ቀን በፊት በአክሲዮን ማህበሩ ዋና መ/ቤት በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡ ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

3.2. የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጪ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀኑ ያላለፈበት መታወቂያ(ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

የልዩ ማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽን አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ፡፡

ከሠላምታ ጋር

አየለ በጋለ
የቦርድ ሰብሳቢ ተመንበር